STAY DC
Stronger Together by Assisting You

# ለማመልከቻ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

**አጠቃላይ እይታ**

በቂ የሆነ ደጋፊ ሰነድ የማመልከቻ ሂደቱ አስፈላጊ ክፍል ነዉ ምክንያቱም በፕሮግራሙ ዉስጥ የእርስዎን ብቁነት ለማረጋገጥ ለዲስትሪክቱ መሰረት ይሆነዋል። ይህ ሰነድ ታስቦ የተዘጋጀው ለSTAY DC ፕሮግራም የሰነድ መስፈርቶች አጠቃላይ እይታ እንዲያገኙ ለማድረግ ነዉ።

በድንገተኛ የኪራይ እርዳታ ፕሮግራም ስር ያለዉ የU.S. ግምጃ ቤት መመሪያ መሰረት፣ ብቁ ለመሆን አንድ ቤተሰብ በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ሲኖር የቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ አለበት እንዲሁም ድጎማ ያገኘዉ ሰዉ  ግዴታ ማወቅ ያለበት፡

## መስፈርት #1

በቤተሰብ ዉስጥ ያለ አንድ ግለሰብ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች ለስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች  ብቁ ሆነዉ ተገኝተዋል ወይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት፣ በቤተሰባቸዉ ገቢ ላይ ማሽቆልቆል ታይቷል፣ጉልህ የሆኑ ወጪዎች ገጥሟቸዋል ወይም ሌላ የገንዘብ እጥረት አጋጥሟቸዋል፤ እንዲሁም

## መስፈርት #2

በቤተሰብ ዉስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች የመኖሪያ ቤት አልባነት ወይም የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት ሊያጋጥማቸዉ ይችላል፤ እንዲሁም

## መስፈርት #3

ቤተሰቡ ያለዉ **የቤተሰብ ገቢ አማካይ የአካባቢ ገቢ መጠን ወይም 80% በታች ነዉ።**

በዚህም ምክንያት፣ የማመልከቻ ጥያቄዎቹን ከመሙላት በተጨማሪ፣ የተሟላ ማመልከቻ ለማግኘት የሚከተሉት ሰነዶች እንዲጨኑ ይጠይቃል፤

1. የማንነት ማረጋገጫ፣
2. የኪራይ ግዴታ ማረጋገጫ፣
3. የገንዘብ ተጽእኖ ማረጋገጫ፣
4. የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት ወይም የቤት አልባነት አደጋ ማረጋገጫ፣
5. የገቢ መመዘኛ ማረጋገጫ፣

ተቀባይነት ያላቸዉ የእያንዳንዱ የሰነድ አይነት ፎርሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል። ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ እነዚህ ምሳሌዎች በምርጫ ቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል። በተጨማሪም የብቁነት ማረጋገጫ መስፈርቶችን በአጥጋቢ ሁኔታ ለማሟላት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሰነድ አይነቶች ሊያስፈልጉ ይችላሉ።

በተመረጡ አጋጣሚዎች፣ የጽሁፍ ማረጋገጫዎች መደበኛዉን ደጋፊ ሰነድ እንዲተኩ ተቀባይነት ሊኖራቸዉ ይችላል።
ይሁን እንጂ፣ ማስታወስ ያለብዎት ነገር የማረጋገጫዎቹን ትክክለኛነት ለማወቅ የፕሮግራም ኤጀንቱ እንዲገኝ በማድረግ ተጨማሪ ማረጋገጫ ያስፈልጋል እና/ወይም የማስፈጸሚያዉ ጊዜ እንዲዳትት ሊያደርግ ይችላል ።

**ማስታወሻ፡** ሰነዱ በሚከተሉት በየትኛዎቹም የፋይል ዓይነቶች ተቀባይነት ያገኛል፡ doc, docx, pdf, xls, xlsx, jpg, ወይም png።
እያንዳንዱ ፋይል ሲጫን በ20 MB መጠን ይገደባል።

ስለ ሰነዱ መስፈርቶች ማንኛዉም አይነት ጥያቄ ካለዎት፣ የፕሮግራሙን ድረ ገጽ በ stay.dc.gov ላይ ይጎብኙ፤ ወይም  የግንኙነት ማእከሉን በ**833-4-STAYDC (833-478-2932) ላይ ከ 7am እስከ 7pm ET- ከሰኞ እስከ አርብ መደወል ይችላሉ።**

## የማንነት ማረጋገጫ

ሊኖር የሚችል የማጭበርበር አደጋን ለመቀነስ፣ የSTAY DC ፕሮግራም ወደዚህ ፕሮግራም የሚያመለክት የእያንዳንዱን ግለሰብ ማንነት ለማረጋገጥ ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል።

**ማስታወሻ:** በ STAY DC ፕሮግራም ስር ለማመልከት ወይም ድጋፍ ለማግኘት የu.s. ዜግነት ያለዉ ወይም ህጋዊ ቋሚ ነዋሪ መሆን አይጠበቅብዎትም።

ማንነትን ለማረጋገጥ፣ ዋናው አመልካች ከእነዚህ የሰነድ አይነቶች ዉስጥ **አንዱ** ሊኖረዉ ያስፈልጋል።

- ህጋዊ (ወይም ጊዜው ያለፈ ስምንት አመት ወይም ከዚያ በታች) የመንጃ ፈቃድ ፎቶ ወይም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ወይም ሌላ ስቴት ፈቃድ የተሰጠ የፎቶ መታወቂያ ካርድ
- አለም አቀፍ ፓስፖርት ወይም ህጋዊ የሆነ ወይም ጊዜው ያለፈበት 5 አመት ወይም ከዚያ በታች የፓስፖርት ካርድ
- የU.S. ቋሚ የነዋሪነት ካርድ ወይም የውጭ አገር ተወላጅ ምዝገባ ደረሰኝ ካርድ
- የU.S. መንግስት ወይም ወታደራዊ የጦር ሀይል ላይ የተደገፈ ማስታወቂያ
- ከu.s. ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ፣ ቴክኒካል ኮሌጅ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰጠ ህጋዊ  የፎቶ መታወቂያ ካርድ። ካርዱ ስምዎን እና ፎቶዎን የያዘ መሆን አለበት
- መረጋገጥ የሚችል ፎቶ ወይም እንደ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ጾታ፣ ቁመት፣ የአይን ቀለም፣ እና አድራሻ የመሳሰሉ መረጃዎች የያዘ ከሆነ በአሰሪው የወጣ መታወቂያ ካርድ

## የኪራይ ግዴታ ማረጋገጫ

በድንገተኛ የኪራይ እርዳታ ፕሮግራም ስር ያለዉ የU.S. ግምጃ ቤት መመሪያ መሰረት፣ አንድ ቤተሰብ በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ሲኖር የቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ አለበት። የኪራይ ግዴታ ማረጋገጫ ከሚከተሉት ዉስጥ **አንዱን** ያጠቃልላል፤

### በጽሑፍ ያለ የኪራይ ወይም የሊዝ ስምምነት ወይም የሰብሊዝ ስምምነት

ለአመልካቹ በምክንያታዊነት የሚቀርብ ከሆነ፣ በአመልካችና በአከራይ ወይም ሰብሊዙን በተቀበለዉ ሰዉ ተፈርሞ በጽሁፍ የሆነ ሊዝ በአመልካች በኩል መቅረብ አለበት፤ እንዲሁም አመልካቹ ድጋፍ ለፈለገበት ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል። ሊዙ የአከራዩን፣ የተከራዩን፣ የኪራይ ክፍሉን አድራሻ፣ ሊዙ ተግባራዊ የተደረገበት ቀን እና የሚከፈለዉ የኪራይ መጠንን ማወቅ አለበት። በተጨማሪም፣ ስምምነቱ የፍጆታ ክፍያዎች ከኪራይ ክፍያ ጋር አብሮ እንደሚካተት ወይም እንደማይካተት ማሳወቅ ይኖርበታል።

### በጽሑፍ ያልሆነ የኪራይ ወይም የሊዝ ስምምነት ወይም የሰብሊዝ ስምምነት

በጽሁፍ ያልሆነ ሊዝ ካለ ወይም አመልካቹ በጽሁፍ ያለዉን የሊዝ ግልባጭ ምክንያታዊ ሆኖ ማግኘት ካልቻለ፣ አመልካቹ የመኖሪያ ቤትና የኪራይ ክፍያ መጠን ሰነድ በሚከተለዉ አድርጎ ማቅረብ አለበት፡

- **የባንክ መግለጫዎች፣ ቼክ፣ ወይም የኪራይ ክፍያ ሂደትን በምክንያታዊነት የሚያሳይ ሌላ ሰነድ**
- **የኪራይ ቤት ክፍሉ ህጋዊ ባለቤት ወይም የአስተዳደር ኤጀንት መሆኑን ማረጋገጥ በሚችል የጉዳይ ሰራተኛ፣ የመንግስት ኤጀንሲ ወይም በመኖሪያ ቤት አቅራቢ የቀረበ በጽሁፍ ያለ ማረጋገጫ**

ማረጋገጫዉ የአከራዩን፣ የተከራዩን፣ የኪራይ ክፍሉን አድራሻ፣ ሊዙ ተግባራዊ የተደረገበት ቀን እና የሚከፈለዉ የኪራይ መጠን ማሳወቅ አለበት። በተጨማሪም፣ ማረጋገጫዉ የፍጆታ ክፍያዎች ከኪራይ ክፍያ ጋር አብሮ እንደሚካተት ወይም እንደማይካተት ማሳወቅ ይኖርበታል።

### የራስ ማረጋገጫ

አመልካቹ የመኖሪያ ቤቱን ሰነድ ማቅረብ የሚችል ሆኖ ግን የኪራይ ክፍያ መጠኑን ሰነድ ማቅረብ ካልቻለ፣ አመልካቹ የአከራዩን፣ የተከራዩን፣ የኪራይ ክፍሉን አድራሻ፣ ሊዙ ተግባራዊ የተደረገበት ቀን እና የሚከፈለዉ የኪራይ መጠንን በጽሁፍ በሆነ የራስ ማረጋገጫ ሊያቀርብ ይችላል። በተጨማሪም፣ ማረጋገጫዉ የፍጆታ ክፍያዎች ከኪራይ ክፍያ ጋር አብሮ እንደሚካተት ወይም እንደማይካተት ማሳወቅ ይኖርበታል።

**በድጋፉ ላይ ስላሉት ገደቦች።** በግምጃ ቤት መመሪያ መሰረት፣ የኪራይ ግዴታን ለማሳየት የራስ ማረጋገጫን መጠቀም ወርሃዊ ከፍተኛዉ 100% ፍትሃዊ የገበያ ኪራይ ወይም የትንሽ አካባቢ ፍትሃዊ የገበያ ኪራይ ከሁለቱ ትልቁ የሚሆነዉን ክፍያ አመልካቹ ለሚኖርበት አካባቢ በቅርቡ በHUD እንደተገለፀው እና በ https://www.huduser.gov/portal/datasets/fmr.html ላይ እንደሚገኘዉ ክፍያዎች ገደብ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፤ እንዲሁም

## መስፈርት #1: የገንዘብ ተጽእኖ መመዘኛ

አንድ አመልካች የኮቪድን የገንዘብ ተጽእኖ ከእነዚህ ዉስጥ **በአንዱ** ማሳየት ይችላል፤

- ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች መመዘኛ
- የቤተሰብ ገቢ ማሽቆልቆል
- ጉልህ የሆኑ ወጪዎች ማጋጠም
- ሌላ የገንዘብ እጥረት

ለእያንዳንዱ ምድብ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን **አንዱን** ያጠቃልላል፡፤

### የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች

- የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች መስጫ ደብዳቤ
- ስለ ስራ አጥነት መመዘኛ አስፈላጊ እዉቀት ያለዉ የጉዳይ ሰራተኛ ወይም የመንግስት ኤጀንሲ በኩል በጽሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ

### የቤተሰብ ገቢ ማሽቆልቆል

- ከገቢ ማሽቆልቆል በፊትና በኋላ ያሉ የክፍያ መጠየቂያዎች
- በኮቪድ ምክንያት የቤተሰብ ገቢ ማሽቆልቆልን የሚያሳይ በጽሁፍ ከቀጣሪ የቀረበ ማረጋገጫ ወይም ደብዳቤ
- በኮቪድ ምክንያት የቤተሰብ የገቢ ማሽቆልቆልን የሚያሳይ የራስ ማረጋገጫ

### ጉልህ ወጪዎች

- ቤተሰብዎ በኮቪድ ምክንያት ያጋጠመዉ የህክምና፣ የልጅ እንክብካቤ፣ የትራንስፖርት፣ የቀብር/የቀብር አፈጻጸም ወጪዎች ወይም ሌሎች ጉልህ ወጪዎች
- በኮቪድ ምክንያት ስለ ስራ ጉልህ ወጪዎች አስፈላጊ እዉቀት ያለዉ የጉዳይ ሰራተኛ ወይም የመንግስት ኤጀንሲ በኩል በጽሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ
- በኮቪድ ምክንያት የቤተሰብ ገቢ ማሽቆልቆልን የሚያሳይ የራስ ማረጋገጫ

### ሌላ የገንዘብ እጥረት

- የፈቃድ ወይም የሽልማት ደብዳቤ ለፌዴራል፣ ለክልል ወይም ለአካባቢ መንግስት የድጋፍ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ፡- Medicaid, SNAP, TANF)
- ስለገንዘብ እጥረት አስፈላጊ እዉቀት ያለዉ ቀጣሪ፣ በጉዳይ ሰራተኛ ወይም በመንግስት ኤጀንሲ በኩል በጽሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ
- ልጆችን፣ አረጋዊያንን ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸዉን የቤተሰብ አባላት ለመንከባከብ ተብሎ ስራ መልቀቅን የሚያሳይ የራስ ማረጋገጫ
- አደጋ ላይ ያለ ቡድን መኖር ወይም አደጋ ባለዉ ቡድን ዉስጥ ባለ የቤተሰብ አባል ተብሎ ስራ መልቀቅን የሚያሳይ የራስ ማረጋገጫ

## መስፈርት #2: የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት ወይም የቤት አልባነት መመዘኛ

ተግባሩ የሚፈልገዉ በቤት ዉስጥ ያለ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ግለሰቦች ቤት አልባ የመሆን ወይም የቤት አለመረጋጋት አደጋ ዉስጥ መሆናቸውን ሊያሳይ ይችላል፣ ይህም ሊያጠቃልል የሚችለዉ (1) ያልተከፈለ ያለፈ የፍጆታ ወይም የኪራይ ገንዘብ ማሳሰቢያ ወይም ከቤት የማስወጣት ማሳወቂያ (2) ደህንነቱ ያልተጠበቀ ወይም ለጤና ጎጂ የሆነ የአኗኗር ሁኔታዎች ወይም (3) ድጎማ ባገኘዉ ሰዉ የታወቀ ሌላ ማንኛዉም አደጋ ሊያደርስ የሚችል ማስረጃ

**ቀኑ ያለፈ የፍጆታ ወይም የኪራይ ማሳወቂያ ወይም ከቤት የማስወጣት ማሳወቂያ**

- ቀኑ ያለፈ የፍጆታ ክፍያ ቅጂ
- ቀኑ ያለፈ የኪራይ ማሳወቂያ ቅጂ
- የቤት ማስለቀቂያ ማስታወቂያ ቅጅ፣ የማስለቀቂያ ክስ ማስታወቂያ ወይም የኪራይ ክፍያ ባለመክፈሉ የፍርድ ቤት ችሎት ቀን
- በቅርብ ያለ የኪራይ ቅጂ እና የቤተሰብዎን ገቢ ከ50% በላይ ለኪራይ እንዳዋሉት የሚያሳይ የፍጆታ ሂሳብ (ይህን ዉሳኔ ለእርስዎ ለማድረግ ገቢዎትንና የክራይ መረጃዎን ከማመልከቻዉ ላይ እንጠቀማለን)።
- የእርስዎን የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት ወይም የቤት አልባነት የሚዳስስ ከመኖሪያ ቤት አቅራቢ፣ ከጉዳይ ሰራተኛ ወይም ከመንግስት ኤጀንሲ በጽሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ  ማረጋገጫዎች በድርጅቱ የደብዳቤ ርእስ ሆኖ መምጣት አለበት (በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ሁሉ) እንዲሁም ቢያንስ ማጠቃለል ያለበት ያረጋገጠዉ ሰዉ ስም፣ የስራ ደረጃ፣ የድርጅቱ ስም፣ የአድራሻ ስልክ ቁጥር፣ የኢሜይል አድራሻ እና ስለእርስዎ ወይም ስለቤተሰብዎ አባል(አባላት) ተዛማጅ መረጃ።
- ለቤት አለመረጋጋትና ቤት አልባነት የቤተሰቡ አደጋ ላይ መሆን

**ደህንነቱ ያልተጠበቀ ወይም ጤናማ ያልሆነ የአኗኗር ሁኔታዎች**

ደህንነቱ ያልተጠበቀ ወይም ጤናማ ያልሆነ የአኗኗር ሁኔታዎች የሚያስረዳ ከመኖሪያ ቤት አቅራቢ፣ ከጉዳይ ሰራተኛ ወይም ከመንግስት ኤጀንሲ በጽሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተለዉ ነዉ፡

- በቂ ያልሆነ ሙቀት፣ ሙቀት አለመኖር ወይም በመሳሪያ መበላሸት ምክንያት የማይሰራ ምድጃ፣ የፍጆታ ክፍያን አለመክፈል፤
- የቧንቧ ዉሃ እጥረት፤
- ለብቻዉ የሆነ የማድቤት አካባቢ እጥረት፤
- ወረራዎች (ለምሳሌ፡- ሻጋታ፣ አይጥ)
- ለሌላ ጊዜ የተላለፈ ከባድ ጥገና፤ እና/ወይም
- ከ1978 በፊት የተገነቡ መዋቅሮች ላይ የቤት ውስጥ ቀለም መላላጥ

ከብዙ በጥቂቱ ሌላ የአደጋ ማስረጃ የሚከተለዉን ያጠቃልላል፤

- “ተደራርቦ” መኖር፣ ሶፋ ላይ መተኛት ወይም በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ሌላ ሰዉ ቤት መተኛት፤
- የቤት ዉስጥ ብጥብጥን መሸሽ ወይም ለመሸሽ መሞከር፤
- መጨናነቅ (ከሁለት(2) በላይ ሰዎች በአንድ አልጋ ላይ ሲተኙ)፤
- ከስቴት ተቋም በቅርቡ መሰናበት፤ ወይም
- ያልተጠበቀ ትንሽ ደረጃ።

STAY DC  ጥገና ለማድረግ ለአከራይ የሚቀርብ የጥያቄዎች ሰነድ፣ ከመንግስት ኤጀንሲ መኖሪያ ቤቱ ለመኖር የማይሆን ወይም ደህንነቱ ያልተጠበቀ እንደሆነ የሚያሳይ ሰነድ፣ ለጭስ ማዉጫ ሂሳብ/ ጭስ ማዉጫዉን ለሚሰራዉ ክፍያ፣ ፎቶግራፎች፣ ከጉዳይ ሰራተኛ ማረጋገጫ፣ የተጠቂ ተሟጋች፣ የመልቀቂያ ወኪል ወዘተ. አይነት ካሉ ማረጋገጫን በመጠየቅ፣ የእነዚህን አደጋዎች የዘፈቀደ ኦዲቶች ይፈጽማል።

## መስፈርት #3: የቤተሰብ ገቢ መመዘኛ

የቤት ውስጥ ገቢ በቤተሰብ ብዛት ውስጥ የተቆጠሩ አዋቂዎች ሁሉ ገቢን ያካትታል። የገቢ ምንጮች ሊሆኑ የሚችሉት ከብዙ በጥቂቱ የሚያጠቃልሉት፡ ደመወዝ፣ ቲፖች፣ ኮሚሽኖች፣ የንግድ ገቢ፣ ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ፣ የሶሻል ሴኪዩሪቲ ጥቅም፣ አመታዊ ክፍያዎች፣ ኢንሹራንስ፣ ሶሻል ሴኪዩሪቲ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች፣ የጡረታ ድጎማ፣ የጡረታ አበል፣ የአካል ጉዳት ወይም የሞት ድጎማዎች፣ የስራ አጥ እና አካል ጉዳት ካሳ፣ የሰራተኛ ካሳና የስራ ስንብት ክፍያ እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድጋፍ ክፍያዎች።

በማመልከቻው ወቅት (1) ዓመታዊ ወይም (2) በየወሩ በሚገኘው የገቢ ምርጫ መሠረት የቤቱን ገቢ በማሳየት ከሚመለከታቸው ሁሉ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሰነድ ዓይነቶች ይፈለጋሉ።

ለእያንዳንዱ የቤተሰቡ ወጣት አባል፣ አመልካቾች የገቢ ሰነድ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

በቤተሰቡ የገቢ ምንጮች ላይ በመመስረት፣ ሰነዱ ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሊያጠቃልል **<u>ይችላል፤</u>**

- ከ IRS ለቤተሰብ ለCY 2020 (የመጀመሪያ ሁለት ገጾች ብቻ) እንደቀረበዉ የፎርም 1040 ቅጂ
- ከIRS ለቤተሰብ ለCY 2020  እንደቀረበዉ የፎርም W-2 ቅጂ
- ከእርስዎ የገንዘብ ተቋም ለCY 2020 ወለድ የሚገኝበት መግለጫ
- የክፍያ ደረሰኞችና ሌላ የደመወዝ መግለጫዎች (ከPayPal፣ Venmo ወይም ለgig ሰራተኞች ከCashApp ክፍያዎች የተጠቃለሉ መግለጫዎች )
- የገቢ ደረሰኝ ሰነድ-እንደ SNAP፣ TANF፣ SSI፣ WIC፣ Head Start እና Medicaid ፕሮግራሞችን የያዘ፣ ብቁ ድጋፍ
- የስራ አጥነት የካሳ መግለጫ
- ከአመት እስከ ቀን የትርፍ/የኪሳራ መግለጫ ወይም የቀጥታ ክፍያዎች ለአገልግሎቶች ወይም ለራስ ስራ የተደረጉ በግል የሚሰሩ ግለሰቦችን አጠቃልሎ የያዘ፣ ከንግድ ወይም ከስራ የተገኘ የገቢ ሰነድ
- የገቢ ተቀማጮችን የሚያሳዩ የባንክ መግለጫዎች
- የSocial Security፣ የዓመታዊ ክፍያዎች፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች፣ የጡረታ ደጎማዎች፣ የጡረታ አበሎች፣ የአካል ጉዳት ወይም የሞት ድጎማዎች እና ሌላ ተመሳሳይ ወቅታዊ ደረሰኞች ሰነድ
- የልጅ ድጋፍ፣የአበል ወይም የአሳዳጊ ክፍያዎች ሰነድ
- ከቀጣሪ ወይም ከመንግስት ኤጀንሲ የተገኘ ደመወዝን ወይም ለቤተሰብ አባል የቀረበዉን የመንግስት ድጋፍ የሚያሳይ በጽሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ
- አሁን ያለዉን የቤተሰብ የገንዘብ ሁኔታና ደጋፊ ሰነዶችን ለማቅረብ አለመቻልን የሚያሳይ ከአመልካቹ የቀረበ የራስ ማረጋገጫ